# እንዴት እንደምትመርጡ

VOTE 2026

***ምርጫዎ የርስዎ ድምጽ ነው – ተመዝገቡ፣ ተረዱ፣ ሂደው ይምረጡ!***

## ማነው መምረጥ የሚችለው?

ሚኖሶታ ውስጥ ለመምረጥ፡ የአሜሪካን ዜጋ መሆን አለብዎ፡ ቢያንስ ቢያንስ ዕድሜዎ፡ ምርጫው በሚካሄድበት ቀን 18 ዓመት መሆን አለበት፡ በሚመርጡበት ዕለት በሚኖሶታ ውስጥ ቢያንስ 20 ቀናት የተቀመጡ መሆን አለብዎ።

በከባድ ወንጀል የተከሰሱ ከሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ በከባድ ወንጀሉ የታሰሩ ካልሆኑ ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

በሌላ ሰው ጥበቃ/ሃላፊነት ስር ሆነውም ዳኛው እንዳትመርጡ ካላገደ በስተቀረ መምረጥ ይችላሉ።

### የ2026 ቀናት

የማጣርያ ምርጫ
ማክሰኞ፡ ነሃሴ 11 ቀን

በአካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ
በፖስታ መምረጥ ወይም በአካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን – ከመስከረም 18ቀን እስከ ህዳር 2 ቀን

ለመምረጥ ተመዝገቡ
በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 13 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።

የምርጫ ቀን
ማክሰኞ ህዳር 3 ቀን

## ለመምረጥ ተመዝገቡ

ለመምረጥ ሲመዘገቡ ባሉበት ወቅታዊ መኖርያ ቤት ኣድራሻ መሆን ኣለበት። ለመመዝገብ ወይም በምዝገባ ወረቀትዎ ላይ ባሉት መረጃዎች ላይ ለመጨመርና የሞሉትን ለማስተካከል ከፈለጉ ወደ mnvotes.gov ይግቡ።

በምርጫው ዕለትም ወደ ምርጫው ጣብያ በመሄድ ለመምረጥ መመዝገብ ይችላሉ። የስሞንና በወቅቱ የሚኖሩበትን መኖርያ ቤት ኣድራሻ የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ማሳየት ኣለቦ።ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ mnvotes.govን ይጎብኑ ወይም በሰልክ ቁጥር 1-877-600-VOTE ይደውሉ።

## ለዓይነት የተዘጋጀውን የምርጫ ወረቀት ተመልከቱ

የቀረቡት ዕጩዎች እነማን መሆናቸውንና በምርጫው ወረቀት ላይ የሚቀርቡትን ጥያቄዎች

ከበስተጀርባ ይቀጥላል...

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

*mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE*

# እንዴት እንደምትመርጡ

*...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ*

ለማየት mnvotes.gov ጎብኙ።

## *ምርጫ የሚካሄድባቸው ቦታዎችና ሰዓቶች*

የት ቦታ ሂደው እንደሚመርጡ ለማወቅ፡ mnvotes.gov.ይጎብኙ። ኣብዛኛዎቹ የምርጫ ቦታዎች በኢትዮጵያ ኣቆጣጠር ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ ምሽቱ 2 ስዓት (በፈረንጆች ኣቆጣጠር ደግሞ ከ7 am. እስከ 8 pm) ክፍት ሆነው ይቆያሉ።

## *ወደ ምርጫው ጣብያ ምን ምማጣት እንደሚገባዎ*

ለመምረጥ ሲመዘገቡ፡ በወቅቱ ያሉበትን የመኖርያ ቤት ኣድራሻ ከሆነ የተጠቀሙት፡ ምንም ዓይነት መታወቅያ ማምጣት ኣያስፈልጎትም። ለመመዝገብ ወይም ሲመዘገቡ የሰጡትን መረጃ ለማሳደስ ከፈለጉ ግን ከመምረጥዎ በፊት፡ የት እንደሚኖሩ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማሳየት ያስፈልጎታል። ስለዚሁ ጉዳይ በበለጠ ለመረዳት mnvotes.gov ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-877-600-VOTE ይደውሉ።.

## *በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከቀኑ በፊት ለሚመርጡ ሰዎች በሚሰጥ ካርድ ምረጡ*

ከዓርብ፡ መስከረም 18 ቀን ጀምረው በኣካባቢዎ ወደ ኣለው የምርጫ ጣብያ በመሄድ ከቀኑ በፊት መምረጥ ይችላሉ። በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከቀኑ በፊት ለሚመርጡ ሰዎች የሚሰጥ የምርጫ ወረቀት በፖስታ እንዲላክሎት መጠየቅ ይችላሉ። የቀበሌዎ የምርጫ ጣብያ የት እንደሆነ ለማወቅና የምርጫ ወረቀት እንዲላክሎ ለመጠየቅ mnvotes.gov.ይጎብኙ።

### *ለመምረጥ ከስራ ፍቃድ ስለማግኘት*

*ለመምረጥ፡ ካለኣንዳች የገንዘብ መቀጮ፡ ከግል ዕረፍትዎም ሆነ ከዓመታዊ ዕረፍትዎ፡ እንዲሆም የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍሉ ሳይጠየቁ ከስራ ወጥቶ የመሄድ መብት ኣሎት።*

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

*mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE*